**ማርች 10/2020 QuickNotes**

## ስለ COVID-19 (ኮሮና ቫይረስ) ዝግጁነት የማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ

በትላንትናው ቀን (ማርች 3)፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል በካውንቲው ስለኮሮና ቫይረስ ዝግጁነት የተደረጉ ጥረቶችን በሚመለከት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት (DHHS) እና ከአስቸኳይ-ክስተት ማኔጅመንት እና ሆምላንድ ሰኩሪቲ ጽ/ቤት መግለጫ አግኝቷል። ካውንስሉ ስለኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወቅታዊ መረጃ በማግኘት የሁሉንም ነዋሪዎች ጤንነት እና ደህንነት ለማረጋገጥ በካውንቲው ስለሚደረጉት ጥረቶች ተነጋግሯል። በዚህ አስፈላጊ ውይይት ላይ የ MCPS መሪዎች እና ሌሎች የማህበረሰብ አጋሮች እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል።

ሁሉም የማህበረሰባችን አባላት መግለጫውን እንዲመለከቱ እና በ መግለጫው ላይ የቀረቡትን ቁልፍ የሆኑ ዶኩመንቶችን እንዲያነቡ እናደፋፍራለን።

በአጠቃላይ ለአሜሪካን ህዝብ ስጋቱ ዝቅተኛ መሆኑን DHHS ከመግለጹም በላይ እስካሁን ድረስ በሜሪላንድ ወይም በናሽናል ካፒታል ሪጅን የተከሰተ-የተረጋገጠ ነገር አለመኖሩ ተገልጿል። በሜሪላንድ ህግ መሠረት፣ ህብረተሰብን የሚያሰጋ የጤና ስጋት ሲከሰት ትምህርት ቤት እንዲዘጋ የሚወስነው በካውንቲው የጤና ኦፊሰር አማካይነት ነው። እነዚህ አይነት ውሳኔዎች የሚሰጡት ከሌሎች የካውንቲው ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር ነው። በዚህ ወቅት፣ በ DHHS መመሪያ መሠረት፣ ትምህርት ቤቶች ክፍት ይሆናሉ እና በካውንቲው ደረጃ መደበኛ ሥራ እንደተለመደዉ ይቀጥላል።

ለማህበረሰብ የተላለፈውን ሙሉ መልእክት ያንብቡ

## ለ MCPS የአመቱ መምህር የመጨረሻ ዙር ሶስት ተወዳዳሪዎች ይፋ ተደረጉ

በማርያን ግሪንባት የትምህርት ገንዘብ ለሚደገፈው ለ 2020–2021 የ MCPS የዓመቱ መምህር ሽልማት ሶስት መምህራን በመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪነት ተሰይመዋል። እነርሱም፡- **አን ሙር/Anne Moore**፣ በፋርምላንድ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት የሙአለህፃናት መምህርት/kindergarten teacher at Farmland Elementary School፣ **ኢንጌ ቺቸስተር/Inge Chichester**፣ በስላይጎ ሚድል ስኩል የዓለም አቀፍ ጥናት ባለሙያ/World Studies content specialist at Sligo Middle School፣ እና **ሮድንይ ቫን ታሰል/Rodney Van Tassell**፣ በዊንስተን ቸርችል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማህበራዊ ጥናት ሪሶርስ መምህር/social studies resource teacher at Winston Churchill High School።

**አን ሙር/Anne Moore** በፋርምላንድ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት/Farmland Elementary School የሙአለህፃናት መምህርት ነች። ሙር/Moore በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ለ23 ዓመት መምህርት ናት። ከብሔራዊ ቦርድ ሠርተፊኬት ያላት መምህርት ስትሆን ተማሪዎች የትምህርት እና ማህበራዊ እድገት እንዲኖራቸው የሚያስችል ከልብ በመነጨ ሁኔታ ትገነባቸዋለች። የእርሷ ክፍል የሚያጓጓ እና ደስታ የተሞላበት

ስፍራ ነው። ስለማስተማር ፅንሰሃሳብ ያላት ችሎታ/ክህሎት በቀላሉ የላቀ እና የመጠቀ ነው። ልጆቻቸው በትምህርት ቤት ስለሚያደርጉት ድርጊት/አፈጻጸም፣ ወቅታዊ ግብረመልስ እና ያሻሻሉትን እርምጃ በቤት ውስጥ እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ፍንጭ በመስጠት ከወላጆች ጋር ያለመታከት ግንኙነት ታደርጋለች። የስነጽሑፍ ፍቅርን ለማዳበር እና የጽሑፍ ችሎታን ኮትኩታ ለማሳደግ “writing workshop” የተሰኘ አውድ ፈጥራለች። በዓመቱ መጨረሻ ላይ ደራሲዎች የሚገኙበት ዝግጅት በማዘጋጀት ተማሪዎች ጽሑፎቻቸውን ያቀርባሉ። ለአካደሚያዊ ትምህርት ስኬታማነት ካላት ቁርጠኝነት የተነሣ ለአንደኛ እና ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በሠመር ወቅት የምንባብ ፕሮግራም ስፖንሰር በማድረግ ተግባራዊ ታደርጋለች። በምታስተምርበት ክፍል ዳታ/መረጃ በመስጠት ጥበበኛ፣ቀልጣፋ፣ስልጡን ናት። ህብረት ዳታ/መረጃ እና እቅድ ላይ የምታደርገው ትኩረት የእርሷ 25 ተማሪዎች ፊደላትን እና የድምፅ ልሳናትን በመለየት ፊደላትን ከድምጽ ጋር በማገናኘት የክፍል-ደረጃን እንዲያሟሉ አስችሏቸዋል። እንደዚሁም ለበርካታ ተማሪ መምህራን አማካሪ ከመሆኗም በተጨማሪ በውትድርና ያገለገሉ መምህራንንም ረድታለች። ሙር/Moore የሙአለ ህፃናት ቡድን መሪ በመሆን፣ የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕላን እና የመስክ ኮሚቴ፣ እንዲሁም የ PTA ሠራተኞች አገናኝ/liaison በመሆን አገልግላለች።

—“ወ.ት/Ms. ሙር/Moore ህጻን ልጅ መግባት ያለበት አይነት ትምህርት ቤትን ለማሳወቅ ምርጥ ተምሳሌት ናት!" ራሄል ለንማን/Rachel Lanman የተባሉ ወላጅ እንደጻፉት።

**እንጌ ቺቼስተር/Inge Chichester** በስላይጎ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Sligo Middle School አለም አቀፋዊ ጥናት የይዘት ባለሙያ ናት። ከተማሪዎቿ ታላቅነትን የምትጠብቅ እና ስለ እነርሱ ጠንካራ አቀንቃኝ ነች። የምትደግፋቸውንም ያክል ተጠያቂም ታደርጋቸዋለች። ታዳምጣቸዋለች፣ እናም የራሳቸውን እድገት እና ብቃት እንዲያዩ እና እንዲያምኑ የማድረግ ልዩ ችሎታ አላት። ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ስለ ራስ እንክብካቤ እና ስልቶች/ስትራቴጂዎች ከእነርሱ ጋር ትነጋገራለች። ርህራሄን ወደ ሥራዋ ይዛ ትመጣለች እናም አካዴሚያዊ ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎችን በንቃት ትፈልጋለች። ሁሌም ጠዋት ጠዋት ተማሪዎች በዋናው በሮች ሲገቡ በድምጽ ማጉያ ለሁሉም ሰላምታ ትሰጣቸዋለች። ከእያንዳንዱን ተማሪ ጋር የሚኖራትን ንግግር/ውይይት የምትደመድመዉ ‘I love you to life!’ / ‘በሕይወቴ ዘመን ሁሉ እወዳችኋለሁ!’ በሚለዉ መሪ ቃሏ ነዉ። የመማሪያ ክፍሏ የቤተሰብነት ስሜት አለዉ። በእቅድ ስብሰባዎች ላይ፣ መምህራን በክፍል ውስጥ ተጋፋጭ እንዲሆኑ ታደፋፍራቸዋለች፣ እናም “በቂ” የሆኑ ትምህርቶችን እንዲያቀርቡ ትገፋፋቸዋለች። ዘወትር ጥያቄዎችን ትጠይቃለች — “ለልጆቻችን ይህን የበለጠ እውን/ገሀድ ዓለም ለማድረግ የሚያስችል መንገድ አለ?” "በእነዚህ ላይ ማሻሻያዎች እና ማመቻቸቶችን እንዴት ማድረግ እንችላለን? ” "ይህንን ፅንሰ-ሀሳብ ተማሪዎች በመጀመሪያ ጊዜ የማይረዱ ከሆነ እንደገና ለማስተማር ምን ማድረግ አለብን?” ቺቼስተር የ MCPS የ 19 ዓመት አገልጋይ ጀግና ናት። የሥራ ባልደረቦች፣ ተማሪዎች እና ወላጆች ደማቅ/የላቀች-ኮከብ ብለው ይጠሯታል። አንድ አስተማሪ “አዎንታዊ ተጽኖ ፈጣሪ/contagious positive” በማለት ጠርቷታል/ጠርታታለች፣ በእሷ ዙሪያ ለረጅም ጊዜ ብትቆዩ አንድ ነገር ታገኛላችሁ/ትይዛላችሁ። የት/ቤቱን የስራ ቀን ትመራለች፣ የ 7ኛ ክፍልን ወደ ጁኒየር አቺቭመንት ፋይናንስ ፓርክ የመስክ ጉዞን ታስተባብራለች እንዲሁም ሁለት የአሜሪኮርፕስ በጎ ፈቃደኞችን ታስተናግዳለች።

- "ከተማሪዎቹ ጋር ግንኙነቶችን በምትገነባበት መንገድ ሁል ጊዜም የማደንቃት መምህር ነች... እንጌ/Inge ለተማሪዎች ሠላማዊ፣ ምስጢረኛ/ታማኝ፣ አጋር እና በፍጹም ተስፋ የማትቆርጥ ሰው እንደሆነች ይሰማቸዋል። ለእያንዳንዱ ተማሪዎቿ በየቀኑ፣ ‘I love you to life፣’ / ‘በሕይወቴ ሁሉ እወዳችኋለሁ፣’ እንደምትል የስድስተኛ ክፍል ቡድን መሪ ላዉራ ኮርቬሊ/Laura Corvelli ጽፋለች።

**ሮድኒ ቫን ታሰል/Rodney Van Tassell** ከ 2011 ጀምሮ በዊንስተን ቸርችል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማኅበራዊ ጥናቶች የሪሶርስ መምህር ነው። እንዲሁም በታኮማ ፓርክ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤትም ሰርቷል። በትዕግስት የተሞላ፣ በጥልቀት እና በቋሚነት አዳዲስ ሀሳቦችን የሚሻና በትብብር ችግር ፈቺነቱ ይታወቃል። በፕሮጀክት ላይ የተመሠረተ ትምህርት ሞዴል በማድረግ እና በማስተማር ተማሪን ማዕከል ባደረገ ትምህርት በመምሪያዉ ላይ ትኩረት አምጥቷል። በዚህ አመት፣ የተማሪን ከተማሪ ጋር ተግባቦት/ግንኙነት ያበረታታል ብሎ በማመን፣ የተማሪዎችን ዴስክ በአራት ክፈፎች አደራጅቷል። ትምህርቶቹ አስደሳች እና የፈጠራ ናቸው። በአሜሪካ እና በታላቋ ብሪታንያ መካከል የመለያያ ዘፈን/መዝሙር ተማሪዎች እንዲጽፉ አድርጓል፤እንዲሁም ቶማስ ጀፈርሰን የከንታኪን ዉሳኔ በመፃፉ ተማሪዎች ለፍርድ እንዲያቀርቡት ክፍሉን ወደ የፍርድ ቤትነት ቀይሯል። እነዚህ

ጥረቶች በላቀ ምደባ Advanced Placement (AP) በዩ. ኤስ. የታሪክ ፈተናዎች እና በሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምዘናዎች ከፍተኛ ውጤት አስገኝቷል። ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ፣ የ AP ዩ. ኤስ. ታሪክ እና የስነ-ልቦና መርሃግብሮችን በ 300 ፐርሰንት ያህል ከማሳደጉም በላይ፣ ዉጤቶች በአማካይ ከ3.5 ወደ 4.1 ማደጉን ተመልክቷል። እንዲሁም የ Churchill የዋና እና ሰመጣ የረዥም ጊዜ አሰልጣኝ፣ እና በርካታ All American፣ All-County and All-Met አትሌቶችን አሰልጥኗል።

- "ጥሩ መምህር ክፍሉን እንድታልፍ/እንድታልፊ በበቂ ሁኔታ የሚያስተምር/የምታስተምር ሰው ነው፣ ግን እንደ ሚስተር ቫን ታሴል ያለ ታላቅ አስተማሪ፣ ትምህርቱን እንድትወድ/ጂ እና በየቀኑ ወደ ክፍል መምጣት እንድትፈልግ/እንድትፈልጊ ያደርጋል፣" ስትል ተማሪ ኤምሊ አብራምሳን/Emily Abramson ጽፋለች።

የ Greenblatt Education Fund/የግሪንብላት የትምህርት ፈንድ በተጨማሪ፣**Joanna Martinez-Mack ን**፣ በጁልየስ ዌስት መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሳይንስ አስተማሪ፣ የ2020 Rising Star Teacher/ብቅ ያለች ኮከብ ብሎ በመሰየም ክብር ይሰጣል። ይህ ሽልማት የፈጠራ ችሎታቸውና ጉጉታቸው ተማሪዎች ራሳቸዉን እንዲያነሳሱ ተጨማሪ ግኝት እንዲያመጡ የሚያበረታታ ከኣምስት ኣመት በታች ልምድ ያላቸውን መምህራን ያከብራል።

ለኣመታዊ መምህር ሽልማት የመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪዎች፣ በ Montgomery County ኣምስት አመት ወይም ከዚያ በላይ የማስተማር ተሞክሮ እንዲኖራቸው የሚገባ፣ በመምህራን ቡድን፣ በትምህርት ቦርድ ኣባሎች፣ በMCPS ሰራተኛ አባሎችና የ Montgomery County Council of PTAs ተወካዮች፣ እንዲሁም በ Greenblatt የቤተሰብ አባላት ቃለ መጠይቅ ይደረግላቸዋል።

መምህራን፣ ከሌሎችም የ MCPS ሠራተኞች እና ኢጋሮች ጋር ስላበረከቱት አስደናቂ ሥራቸው በ ልጆች ሽልማት ክብረ በአል/Children Awards Celebration አካል ዓመታዊ ሻምፒዮና በመሆን ይሸለማሉ። የ MCPS የአመቱ መምህር፣ ሰኞ፣ ኤፕሪል 27 በ Bethesda Blues & Jazz Supper Club በቤተዚዳ በሚካሄደው ክውነት ወቅት ይሰየማል።

የ Marian Greenblatt Fund፣ በቀድሞ የትምህርት ቦርድ ኣባል ስም የተሰየመ፣ ተማሪዎቻቸውን ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያነቃቁ፣ ወጣት አስተማሪዎች ሊሆኑ ከሚችሉት በላይ የተሻሉ እንዲሆኑ የሚያበረታታ እና ትምህርት ቤታቸውን እና ማህበረሰባቸውን ለሚረዱ ዕውቅና ይሰጣል። ድርጅቱ ለእያንዳንዱ የዓመቱ መምህር የመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪ የ$2,000 ሽልማት፣ እና ለ Rising Star መምህር $1,000 ይሸልማል።

### *ሥር የሰደደ ከትምህርት መቅረትን መቀነስ፦ እያንዳንዱ ቀን ዋጋ አለዉ*

በየዓመቱ ከ 8 ሚሊዮን በላይ የዩ.ኤስ.ተማሪዎች አንድ ወር ያህል ትምህርት ቤት እንደማይመጡ/ቀሪ እንደሚሆኑ ያውቃሉ? ሥር የሰደደ ከትምህርት መቅረት በመላ አገሪቱ ውስጥ እያደገ የመጣ ችግር ነው፣ እና MCPS ም ከችግሩ ነፃ አይደለም።

በየቀኑ ትምህርት ቤት መከታተል በእርግጥ ወሳኝ ነዉ።

የትምህርት ቤት ስኬት ከጥሩ ክትትል ጋር አብሮ ይሄዳል። ወደ ስፕሪንግ እረፍት እየተቃረብን፣ ልጆቻቸው በየቀኑ ትምህርት ቤት መከታተላቸዉን እንዲያረጋግጡ ወላጆች ይበረታታሉ። እረፍትን በጥቂት ቀናት ማራዘም አጓጊ/የሚፈታተን እንደሆነ እናውቃለን፣ ነገር ግን ያስታውሱ፣ እነዚያ ቀናት እንደ ቀሪዎች ይቆጠራሉ። ምንም እንኳን ቀሪዎቹ የተፈቀዱ መቅረቶችም ቢሆኑ፣ በዚህ እና በዚያ ጥቂት ያመለጡ ቀናት፣ በጣም ብዙ የተሳቱ የትምህርት ጊዜን ሊጨምሩ እና ልጅዎን በት/ቤት ወደ ኋላ ሊያስቀሩ ይችላሉ።

ለልጅዎ ዘወትር የትምህርት ክትትል ስጦታ ይስጡ(ጧ)ት እና ዘወትር የመከታተል ልምድን ለመገንባት ይርዱ።

**ከምናዉቀዉ**

ቀሪዎቹ የተፈቀዱም ይሁኑ ያልተፈቀዱ፣ አንድ ተማሪ የትምህርት ዓመቱን 10 በመቶ (18 ቀናት) ወይም ከዚያ በላይ ከቀረ/ች ሥር የሰደደ ቀሪ ነዉ/ናት።

- በሁሉም ዕድሜ፣ ዘር እና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ልጆች ሥር የሰደዱ ቀሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን በጣም ተጋላጭ የሆኑት በድህነት የሚኖሩ እና ቤት አልባ የሆኑ ልጆች ናቸው።
- በሰፕቴምበር ወር ከሁለት እስከ አራት ቀናት ቀሪ ከሚሆኑት ተማሪዎች መካከል ግማሽ የሚሆኑት ወደ አንድ ወር ያህል ከትምህርት ቤት መቅረታቸውን ይቀጥላሉ።
- በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት፣ በመዋዕለ ሕጻናት እና በአንደኛው ክፍል ውስጥ ሥር የሰደዱ ቀሪዎች ሦስተኛ ክፍል ላይ በክፍል ደረጃ የማንበብ ዕድላቸው በጣም አነስተኛ ነው።
- በሦስተኛ ክፍል መጨረሻ ላይ በክፍል ደረጃ ማንበብ የማይችሉ ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጥሎ በመዉጣት/በመልቀቅ ብቃት ካላቸው አንባቢዎች በአራት እጥፍ ይበልጣሉ።
- ስድስተኛ ክፍል ላይ፣ ሥር የሰደደ መቅረት አንድ ተማሪ ከሁለተኛ ደረጃ ደረጃ ት/ቤት ጥሎ ለመዉጣት/ለመልቀቅ ዋና አመላካች ይሆናል።

በትምህርት ቤት ለመከታተል የሚቸገር/የምትቸገር ልጅ ካወቁ፣ የ Pupil Personnel and Attendance Services/የፒፐል ፐርሶኔል እና የተማሪ አገልግሎቶች ክፍልን በስልክ ቁጥር 240-740-5620 ያነጋግሩ።

**የልዩ ትምህርት ጠቅላላ ጉባዔ ሜይ 2 እንደሚሆን ተወሰኗል**

የ MCPS ወላጆች፣ የሥራ ባልደረቦች እና የማህበረሰብ አባላት "Leading the Way Today, Partnering for a Better Tomorrow" ለተሰኘው ሰባተኛዉ ዓመታዊ የልዩ ትምህርት ጉባዔ ተጋብዘዋል። ጉባዔዉ ከ 8:15 a.m.–1 p.m. **ቅዳሜ፣ ሜይ 2** በኩዊንስ ኦርቻርድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Quince Orchard High School, 15800 Quince Orchard Road in Gaithersburg ይካሄዳል።

የ Center for Inclusive and Special Education ዳይሬክተር፣ እና በ Graduate School of Education at Lesley University ተባባሪ ዲን የሆኑት Patricia Crain de Galarce, Ed.D./ዶ/ር ፓትሪሺያ ክሬይን ዲ ጋሌርስ፣ ዋና የንግግር አቅራቢ ይሆናሉ።

ወላጆች/ሞግዚቶች፣ የትምህርት ባለሙያዎች እና የማህበረሰብ አጋሮች የልዩ ትምህርት ጉባዔዉን በነፃ እንዲሳተፉ ክፍት ነው። የህፃናት እንክብካቤ፣ ቀላል ቁርስ እና የማስተርጎም አገልግሎት ይሰጣል።

ተጨማሪ መረጃ

ለመሣተፍ ይመዝገቡ.

**ምስል የተለጠፈበት ማስታወቂያ/ፖስተር ውድድር K–12 ላሉ ተማሪዎች ተከፍቷል**

እንደ ኤዥያን አሜሪካን እና ፓስፊክ አይላንደርስ/ደሴት የቅርስ ወር አካል በመሆን፣ የኤዥያን ፓስፊክ አሜሪካን የተማሪ ስኬት ተግባር/ድርጊት ቡድን (APASAAG) ለ K-12 ተማሪዎች የፖስተር ውድድር ድጋፍ/ስፖንሰር እያደረገ ነው።

ውድድሩ ተማሪዎች ታዋቂ የሆነ/ች ኗሪ ወይም የሞተ/ች ኤዥያን አሜሪካንን እንዲለዩ፣ እና የዚያን ሰው አምሳያ እና አስተዋፅ የሚወክሉ ምስሎችን የሚይዝ የስነጥበብ ስራ እንዲፈጥሩ ይጠይቃል።

አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃ አሸናፊዎች ለእያንዳንዱ አንደኛ ደረጃ፣ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደረጃዎች የገንዘብ ሽልማት ያገኛሉ።

**የሚቀርቡት ሥራዎች ረቡዕ ፣ ኤፐሪል 1 ገቢ መደረግ/መላክ አለባቸው።**

ለዉድድሩ ከ APASAAG ጋር በመሆን፣ the Chinese American Parents Association of Montgomery County, Calvin Li Memorial Foundation, the City of Rockville Asian Pacific American Task Force, the Association of Vietnamese Americans and the Indonesian American Association በትብብርና ድጋፍ ኮ ስፖንሰር አድርገዋል።

ስለ ፖስተር ውድድር ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን/መረጃ

**MCPS ለ Summer RISE አገልጋዮችን ይፈልጋል**

እንደ የ Summer RISE 2020 ፕሮግራም አካል በመሆን ስለ ሚሠሩበት ቦታ እና ስለሚሠሩት የሙያ መስክ ለ MCPS ጁንየሮች እና ሲንየሮች በጁላይ ወር ዉስጥ ከሦስት እስከ አራት ሣምንት ማስተማር ይፈልጋሉ? MCPS በሁሉም የሙያ መስኮች አገልጋዮችን በመፈለግ ላይ ሲሆን፣ ነገርግን በኪነጥበብ እና በመዝናኛ ፣በባዮ ሳይንስ፣ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ሳይበርሰክዩሪቲ ፣ በኢንጂነሪንግ፣ በጤና እንክብካቤ ዘርፍ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በሕግ ዉስጥ ላሉት ልዩ ፍላጎት አለዉ።

የሰመር RISE የ MCPSን ጁንየሮች እና ሲንየሮች ስለ የስራ ዕድሎች እንዲማሩ እና ቀጣሪዎች የወደፊት የስራ ኃይል እንዲገነቡ ያግዛቸዋል።

ስለ ሰመር RISE ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፣የኢንፎርሜሽን ከፍለጊዜ ይከታተሉ እና/ወይም አስተናጋጅ ለመሆን ይመዝገቡ። ያስተናጋጅነት ምዝገባ ማርች 31 ይዘጋል/ያበቃል።

**የ 2019 ዓመታዊ ሪፖርት**

የ 2019 ለማህበረሰብ የተዘጋጀ ዓመታዊ ሪፖርት አሁን ይገኛል። ለማህበረሰብ የቀረበ ዓመታዊ ሪፖርት የ 2018-2019 የትምህርት አመት ትኩረቶችን/ፍንጮችን እና በትምህርት፣ በመሻሻል እርምጃ፣ ስኬታማነት እና እድሎችን አስመልክቶ ስለ ፍትኃዊነት እና ልቀትን በተመለከተ ያለንበትን ያካትታል። ሪፖርቱ ስለማንነታችን፣ ስለተማሪዎች አፈፃፀም መረጃ፣ የሥራ አፈጻጸም መረጃ፣ እና የ MCPS ን ራእይ እና ተልእኮ ለመፈጸም MCPS የወሰዳቸውን እርምጃዎች ለማህበረሰቡ መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን ይሰጣል። አመታዊ ሪፖርት ለመመልከት ይህንን ድረ-ገጽ https://www.montgomeryschoolsmd.org/annualreport/2019/ ይጎብኙ።

**እለቱን ያስታውሱ፡-የፊልም ማጣሪያ፣ ውይይት ለኤፕሪል 16 ተይዟል**

ወላጆችና የማህበረሰብ አባላት Resilience :-The Biology of Stress & the Science of Hope_ለተሰኘዉ የፊልም ማጣሪያ ሐሙስ፣ ኤፕሪል 16 ተጋብዘዋል።

ዝግጅቱ የሚከናወነው ከ 7–8:30 p.m. በ ኖርዝዌስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Northwest High School auditorium, 13501 Richter Farm Road in Germantown ነዉ።

ከፊልሙ ማጣሪያ በኋላ፣ ችግርን ማሸነፍ እና ጥንካሬን ማጎልበት በሚል ርዕስ ላይ የፓናል ውይይት ይደረጋል።

**በአካባቢ ፖለቲካ ፍላጎት አለህ/ሽ? "Councilmember for a Day" አባል ለመሆን አመልክት/ቺ ለአንድ ቀን የምክር ቤት አባል ለመሆን ያመልክቱ**

የፖለቲካ ዝንባሌ ያላቸው እና የ Montgomery County Councilmember/የምክርቤት ኣባል ሆነው ማገልገል የሚፈልጉ የ8ኛ፣ 9ኛ፣ 10ኛና 11ኛ ክፍል ተማሪዎች ማመልከቻቸውን ለምክር ቤት ኣባል Craig Rice's "Councilmember for a Day/Challenge/ ገቢ እንዲያደርጉ ተጋብዘዋል። ለመግባት፣ ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመመለስ ቪዲዮ (ሁለት ደቂቃ ወይም ያነሰ) ወይም የድርሰት ጽሑፍ (500 ቃላት ወይም ያነሰ) ለማቅረብ ይችላሉ፦

- ወጣቶችን የሚያጋጥማቸው ከሁሉም በላይ ኣሳሳቢ ህዝባዊ የፖሊቲካ ጉዳይ ምንድን ነው?
- እነዚህን ጉዳዮች እንዴት መፍታት እንዳለባቸው ለአገር አቀፍ፣ ለስቴት፣ እና/ወይም ለአካባቢ መሪዎች ምን አስተያየት ይኖርሃል/ይኖርሻል?

አንድ ተማሪ የክብር የካውንስል አባል በመሆን ይመረጣል/ትመረጣለች እና የካውንስል አባል Rice ጋር በመሆን ቀኑን በሙሉ የሚሰሩትን ያያል/ታያለች። ለአንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃዎች የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል።

የማስገቢያ ቀነ ገደብ በ 5 p.m አርብ፣ ኤፐሪል 3 ኣሸናፊው/ዋ ተማሪ፣ የምክር ቤት የትምህርት ኮሚቴ ሊቀመንበር ሆና ለምታገለግለው፣ ለምክር ቤት ኣባል Craig Rice/ክሬግ ራይስ ብቸኛ መድረሻ ያገኛል/ታገኛለች፣ እናም በቀኑ የምክር ቤቱ የክብር እንግዳ ሁኖ/ና ይዉላል/ትዉላለች።

ማመልከቻዎችን እዚህ ማስገባት ይቻላል

**ለ፦2020 Girl Power ዉድድር የአመልካቾች ጥሪ**

የሴቶችን ታሪካዊ ወር ለማክበር፣ የየሞንትጎመሪ ካውንቲ የሴቶች ኮሚሽን በሦስተኛው ዓመታዊ "Girl Power" ውድድር እንዲሳተፉ ነዋሪዎችን ይጋብዛል።

ከ5 እስከ 105 ዓመት እድሜ መካከል ያሉ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎችየሚያስተናግዱ አጭር ትረካ፣ ግጥም፣ ወይም ስዕል/ንድፍ እንዲያቀርቡ ይበረታታሉ፦ የሴቶችን የመምረጥ መብት 100ኛ ዓመት መታሰቢያ ስናከብር ፣ አሁንም ቢሆን ለሴቶች እና ለልጃገረዶች ምን መሰናክሎች አሉ ብለው ያስባሉ እና እንዴት እነሱን ለማፍረስ ሊረዱ ይችላሉ?

በተለምዶ የሚቀርቡት ሥራዎች አጫጭር ታሪኮች፣ ግጥሞች እና ስዕሎች ናቸው ነገር ግን ፈጠራ ይበረታታል፣ እናም አማራጭ የፈጠራ ገላጭ ሥራዎች ቢቀርቡ ተቀባይነት ይኖራቸዋል። ውድድሩ የሚወሰነው በፈጠራ ችሎታ እና በይዘት ይሆናል፤ ተወዳዳሪዎች የብልግና/አጸያፊ ነገሮችን መጠቀም እና ከዘረኝነት ወይም ጾታዊ ከሆኑ አስተያየቶች ወይም ገጽታዎች መቆጠብ ይኖርባቸዋል። አሸናፊ ሥራዎች በአራት ምድብ ይመረጣሉ ፦አንደኛ ደረጃ ፣ መካከለኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና አዋቂ።

ሁሉም የውድድሩ አሸናፊዎች በሴቶች ኮሚሽን ድረ-ገጽ ላይ ይወጣሉ እና swag ቦርሳ ያገኛሉ፣ ከኮሚሽነሮች ጋር ፎተግራፍ መነሣት፣ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሴቶች ኮሚሽን ስብሰባ ላይ ከሌሎች አሸናፊዎች ጋር በክብር እንግድነት ይጋበዛሉ።

ለአንድ ሰው አንድ ብቻ የተወሰነዉ ሥራ እስከ ማርች 31 ቢቀርብ ተቀባይነት አለው። የጽሑፍ መወዳደሪያ ከ 500 ቃላት መብለጥ የለበትም። የሚቀርቡ ሥራዎች ሙሉ ስም፣ ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ እና ትምህርት ቤት

(የሚመለከተው ከሆነ)፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻ ማካተት አለባቸዉ። አሸናፊዎች ኤፕሪል 30 ይፋ ይደረጋል።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና የውድድር ሥራዎችን በመስመር ላይ ለማስገባት፣ 2020 Girl Power Contest ድረገጽ ይጎብኙ። የውድድር ሥራዎችን በኢ-ሜይል ለ cfwinfo@montgomerycountymd.gov ማስገባት ወይም ወደ 2020 Girl Power Contest, Montgomery County Commission for Women, 21 Maryland Avenue, Suite 330, Rockville, MD 20850 መላክ ይቻላል።

ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች የሚያቀርቡት ሥራ የራሳቸዉ መሆን ያለበት እና ከወላጅ ወይም ከአሳዳጊ የጽሑፍ ፈቃድም አብሮ ሊኖር ይገባል። ሁሉም የሚቀርቡ ሥራዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሴቶች ኮሚሽን ንብረት ይሆናሉ እናም ለማስታወቂያ አላማዎች ጥቅም ላይ ሊዉሉ ይችላሉ።

ውድድሩ ስፖንሰር የሚደረገው በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሴቶች ኮሚሽን፣ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ቤተመጻሕፍት እና የቤተመጻሕፍቱ ወዳጆች፣ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 240-777-8300 ይደውሉ ወይም የ Montgomery County Commission for Women ድረ-ገጽ ይጎብኙ።